# ኢህአዴግን የምመርጥበት ምክንያቶች

መለስ ዓ.

ብዕሬን እንዳነሳ የገፋፋኝ ጥር 2 ቀን 2002 ዓ.ም. ለንባብ በበቃው ሪፖርተር ጋዜጣ «እኔ የምለው» አምድ ሥር «ድምፅ የምሰጠው የኢህአዴግን የ18 ዓመት የሥራ ውጤት ምዘና በማድረግ ነው» በሚል ርዕስ እና በተመሳሳይ አምድ ጥር 8/2002 ዓ.ም. «ለተቃዋሚዎች ድምጽ የማልሰጥበት መሠረታዊ ምክንያቶች» በሚል ርዕስ በሌላ አስተያየት ሰጪ የተዘጋጀ ምላሽ መሰል ጽሁፍ ከተመለከትኩ በኋላ ነው፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ሁለቱም ፀሀፊዎች ያላቸውን አቋም በሰለጠነ መልኩ ማቅረባቸው ይበል የሚያሰኝ ብቻም ሳይሆን ሊበረታታ የሚገባው ነው፡፡ ማንኛውም ሰው ምንም አቋም ይኑረው በሠላማዊ እና ኃላፊነት በተሞላበት መንገድ አቋሙን ማስተላለፍ መሞከሩ የኢትዮጵያ ህዝቦች ለዘመናት ባካሄዱት ትግላቸው ያረጋገጡት መብት ነው፡፡

እኔ በሁለቱም ጽሁፎች ላይ አስተያየቴን በመስጠት ወደራሴ ርዕስ እመለሳለሁ፡፡ ድምጽ የምሰጠው የኢህአዴግን የ18 ዓመት የሥራ ውጤት ምዘና በማድረግ ነው በሚል ርዕስ የቀረበው ጽሁፍ እያንዳንዱ መስመር ላይ ያለውን ስህተት በማንሳት ተገቢውን ምላሽ መስጠት የሚቻል ቢሆንም ይህን ከማድረግ መቆጠቡን ነው የምመርጠው፡፡ ምክንያቱም ፀሐፊው ኢህአዴግ ኤርትራን አስገንጥሏል፣ ድሮ ያልነበረን የጎሣ ፖለቲካ አምጥቷል፣ ክልሎችን አዋቅሮ በሕገ መንግስት አካቷል፣ አንቀጽ 39 ዓባይን በተመለከተ ከግብጽ ጋር ሚስጥራዊ ስምምነት ተፈራርሟል ፈረንጆች ጠላቶቻችን ናቸው፣ የታሪክ ጠላታችን የሆኑት አረቦች በኢኮኖሚ እንዲወሩን አድርጓል በሚል ለሰጡት ውሃ የማይቋጥርና የተልፈሰፈሰ አስተያየት መልስ መስጠት አንባብያንን መናቅ ይሆንብኛል፡፡ ይሁን እንጂ ኢህአዴግ በኢኮኖሚ እና ማኅበራዊ ልማት ክንዋኔ እንዲሁም የሰብአዊ መብቶች መከበር ዙሪያ ፍፁም ወይም እንከን የለሽ ነው የሚል መከራከሪያ ለማቅረብ አይዳዳኝም፡፡

በመጪው ምርጫ እኔን ጨምሮ በርካታ መራጮች ከተቀናቃኝ ፓርቲዎች ይልቅ ኢህአዴግን በነቂስ ወጥተን የምንመርጥበትን ምክንያት ቀስ ብዬ የምመጣበት ከፍ ብሎ በተጠቀሰው ጽሁፍ ላይ ያሉኝን አስተያየት ላስቀድም፡፡ ቢሆንም ጽሁፉ ሁለት

መሠረታዊ ጉድለቶች አሉት:: የመጀመሪያው ጉዳይ ጸሀፊው በአለ ተባለ ያቀረቡት ፅሁፍ ምን ያህል ጨለምተኛ እንደሆኑ የሚያሳይ ነው:: ሁለተኛ ፀሀፊው የኢህአዴግን የ18 ዓመታት የሥራ ውጤት መሠረት በማድረግ ያቀረቡት ምዘና የመቶኛ ስሌት 29 በመቶም ሆነ 90 በመቶ ከምን አንፃር እንደተሠራ የሚያሳይ ባለመሆኑ ሳይንሳዊ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም:: ለተቃዋሚዎች ድምጽ የማልሰጥበት መሠረታዊ ምክንያቶች በሚል ርዕስ ሥር በቀረበው አስተያየት ላይ ፀሐፊው ተቃዋሚዎች የነገ ፓርቲ አይደሉም፣ የማይቃወሙበት ነገር የላቸውም፣ ፀረ-ዲሞክራሲ አቋም አላቸው፣ የኢትዮጵያ ህልውናና ልዕልና ደንታ የሌላቸው በመሆናቸው እንዲሁም አንወክልህለን ለሚሉት ህዝብ ደንታ የሌላቸው ናቸው በሚለው አስተያየት ላይ ብስማማም እኔ ግን ገዥው ፓርቲ እንዲመረጥ የሚያደርጉት ዋነኛ ምክንያቶች ከላይ የተገለፁት የተቀናቃኝ ፓርቲዎቹ ባህሪ ሳይሆን የኢህአዴግ የራሱ ጥንካሬ ነው:: ስለሆነም የኢህአዴግን በመጪው ምርጫ የምንመርጥበት ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው:-

## 1. <u>የጠራ ፖሊሲ እና ስትራቴጂ መኖር</u>

ኢህአዴግ በተለያዩ መስኮች ሀገሪቱን የሚለውጡ ፖሊሲና ስትራቴጂዎችን በማውጣት ወደ ተግባር መለወጥ ችሏል:: የእነዚህ ፖሊሲና ስትራቴጂዎች አልፋና ኦሜጋ አላማቸው ሀገሪቱን ለዘመናት እግር ተወርች አስሮ የቆየውን ኋላቀርነት ታሪክ ማድረግ ነው:: ኢህአዴግ በስልጣን ላይ በቆየበት 18 ዓመት ውስጥ ፈጣን የኢኮኖሚ ልማት በማስመዝገብ የኋላቀርነት እና የድህነት አዘቅት ውስጥ የምትገኘውን ሀገራችን ወደተሻለ የልማት ምዕራፍ እንድትሸጋገር እያደረገ መሆኑን ከቃላት ይልቅ ተግባር ምስክር ነው:: ሀገራችን ባለፉት ጥቂት ዓመታት በትምርት፣ በመንገድ፣ ኃይል ማመንጫ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ግንባታ ወዘተ... መስኮች ያሳየችውን ለውጥ ማየት ብቻ ለፖሊሲዎቹና ስትራቴጂዎች ስኬታማነት አንዱ ማሳያ ነው::

ከሁለት ዓመት በፊት በ12ኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ስብሰባ ለመሳተፍ የመጡ የቻድ የልዑካን ቡድን ለሻይ እረፍት የተ.መ.ድ የስብሰባ አዳራሽ በረንዳ ላይ ሆነው ካዛንቺስ አካባቢ ያለውን የኮንስትራክሽን ግለት /Construction Boom/ ተመልክተው ያነሱልኝ ጥያቄ ኢትዮጵያ ምን አዲስ ነገር አገኘች? የሚል ነበር:: ለዚህ ጥያቄ መልሱ ቀላል ነበር:: ኢህአዴግ የጠራ ፖሊሲና ስትራቴጂ ስላለው ብቻም ሳይሆን ሀገሪቱን የመለወጥ ቁርጠኛ አቋም በመያዙ እንደሆነና ይህ ልማት እንደ በርካታ

የአፍሪካ ሀገሮች በርዕሰ መዲናዎች ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ትናንት ዕርጅና ተጫጭኗቸው በነበሩ የሀገሪቱ ከተሞች የሚስተዋል ሀቅ ነው፡፡ እስቲ ሁላችንም በዚች ወቅት አካባቢያችንን እንቃኝ፡፡ ባለፉት ሰባት ዓመታት ነዳጅ አምራች ካልሆኑ ሀገሮች ውስጥ ከፍተና ኢኮኖሚ በማስመዝገብ ተጠቃሽ ከሆኑ ሀገሮች ውስጥ ኢትዮጵያ አንዷ መሆን ችላለች፡፡

የግል ባለሀብቱ ለስራ የተመቻቸ ሁኔታ ስለተፈጠረለት እና መንግስትም አስፈላጊውን ድጋፍና መረጃ በማቅረብ ለሀገሪቱ ልማት የበኩሉን አስተዋጽኦ እያደረገ ሲሆን ይህም መጪውን ጊዜ የበለጠ ብሩህ ያደርገዋል፡፡ ጌትነት ኃይሌ እና ሂሩት ሃይሌ የተባሉ ተመራማሪዎች በ4ኛው የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ኮንፈረንስ ላይ ባቀረቡት የጥናት ወረቀት ላይ እንደተመለከተው በሀገራችን ከ1983 ዓ.ም ወዲህ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ መሆኑን ጠቅሰው ቀጣይነቱን ግን ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግ አስምረውበታል፡፡ ይህን ዕውን ለማድረግ ደግሞ በኢህአዴግና በህዝቡ ተሳትፎ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ መጪው ምርጫ ለዚህ አይነተኛ ዕድል ይከፍታል፡፡

**2. <u>የኢትዮጵያን የመምራት ብቃት</u>**

የአፍሪካ ቀንድ ግጭት እና ፖለቲካ ትርምስ የሚበዛበት ነው፡፡ በአካባቢው ሀገሮች የሚከሰቱ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች እንደ ሰደድ እሳት ከአንዱ ሀገር ወደ ሌላ የመዛመት ዕድላቸው ሰፊ ነው፡፡ አካባቢው ሶማሊያን የመሰለ መንግስት አልባና የአሸባሪዎች መናኸሪያ የሆነች አገር መኖር ጋር ለመካከለኛው ምሥራቅ የቀረበ መሆኑም ለአደጋ ተጋላጭ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ጁልያ ማክስቲድ የተባሉ ምሁር እ.ኤ.አ ጁላይ 2001 ባደረጉት ጥናት ክልሉ ሰፊ ገበያ እና ዕምቅ የተፈጥሮ ሀብት ቢኖረውም አካባቢው በሠላም ውሎ ማደር እንዳልቻለ ገልፀዋል፡፡ በዚህ ክልል የምትገኘው ሀገራችን በሰሜን የጀብደኛውን የአስመራ ነውጤ፣ የሶማሊያ መፍረስ፣ የሱዳን ሰላም ፈር አለመያዝ ጋር ተያይዞ ሁሌም ስጋት መኖሩ አይቀሬ ነው፡፡ በሃገር ውስጥም የሁሉንም ህዝቦች መብት በማክበር፣ በሰከነ አዕምሮ ሁኔታዎችን በመተንተን ከውስጥም ከውጭም አቅም ያለው ኢህዲግ ብቻ ነው፡፡ ይህ አስተያየት በየትኛውም ወገን ላይ አላስፈላጊ ስጋት ለመፍጠር አይደለም፡፡ ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንኳን ኢትዮጵን የመሰለ ሰፊ ሀገር በቅጡለማስተዳደር ይቅረና እንመራዋለን የሚሉትንም ፓርቲ ዕምነት ተጥሎ የሚሰጣቸው አይደሉም፡፡ ዛሬ አንድ ላይ ቢሆኑም፤ ነገ አንድ ላይ ውለው አያድሩም

በጥላቻና ቂም የተሞሉ ስለሆኑ የዚችን ሀገር ልዕልና ለማረጋገጥ ተቃዋሚዎች አማራጭ አይደሉም::

ለዚህም አብነት የሚሆነው ከኢህአፓ፣ ኢዴፓ እስከ ቅንጅት አንድነት ያለው መሰንጠቅና መሰነጣጠቅ ነው:: መድረኮችም ቢሆን ኢህአዴግን በሃይል ጥሎ ስልጣን ከመያዝ ውጭ ሌላ አላማ የላቸውምና የተጣበቁበት ሙጫ የሚላቀቅበትን ጊዜ መጠበቅ ነው:: እነዚህ ፓርቲዎች በውስጣቸው ለሚፈጠረው ችግር ሁሌም ተጠያቂ የሚያደርጉት ኢህአዴግን ነው:: ኢህአዴግ በውስጥ ፓርቲ ትግል ተተፍተው የሚወጡ ሰዎች ይኑሩት እንጂ ፓርቲው ተከፍሎ ንትርክ ውስጥ የገባበት ወቅት የለም አልነበረም:: ምናልባት ተቃዋሚ ፓርቲዎች ስላላሴሩበት ይሆን?

### 3. <u>ችግርን የማረም ፍላጎት</u>

ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በቅርቡ ለሀገር ወስጥ ጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ ኢህአዴግ ደርግን የማሸነፍ ሚስጥሩ ስህተቶቹን አለመድገሙ እንደሆነ መናገራቸው ትዝ ይለኛል:: ገዢው ፓርቲ ከትጥቅ ትግሉም በኋላ ወደ መቀዛቀዝ በራሱ ቋንቋ ወደ መበስበስ ከገባ በኋላ ችግሮቹን አይቶ ጠንካራ ጎኑን ቀምሮ ለመሄድ አላቅማማም:: በ1997 ምርጫ ላይም በርካታ መራጭ ካርዱን በመንፈግ ቅሬታውን ሲገልጽ ድርጅቱ የሄደው ራሱን ወደማየት እና ስህተቶቹን ወደ መገምገምና ወደ ማረም ነው:: ከዚህ ጊዜ በኋላ ድርጅት በምርጫው ወቅት ለሁለት ዓመት ያስመዘገበውን ድል አከታትሎ በመድገም የመልካም አስተዳደር ችግሮን በአመዛኙ መፍታት ችሏል:: ከዚህ በተቃራኒ ተቃዋሚዎች እንኳንስ አገራዊ ጉዳዩ ቀርቶ ቅንጅት የፈረሰበትን ምክንያት ለመረጣቸው ህዝብ በይፋ ከመንገር ይልቅ የእናቴ መቀነት አደናቀፈኝ በሚል ብሂል እርስ በርስ ሲወነጃጀሉ ነው የሚታዩት :: ኢንጂነር ሃይሉ ሻውልም ሆነ አቶ ልደቱ አያሌው እንደሁም ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የአብዴም ሆነ የእምዬን ማለት አይፈልጉም:: ለነገሩ ከዝንጀሮ ቆንጆ ምን ይመርጧል አይደል የሚባለው::

## 4. በአለም አደባባይ ኢትዮጵያን ከፍ የማድረግ አቅም

የሀገራችን የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ ግሎባላይዜሽን እስከነችግሮቹ የአለማችን ነባራዊ ሁኔታ መሆኑን፣ ችግሮቹን ለመቀነስ እየተጣጣረ በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ አገራዊ ጥቅምንና ደህንነትን ለማረጋገጥ ከመጣጣር ውጭ ሌላ አማራጭ እንደሌለ በግልጽ ያስቀመጣል:: ሀገራችን የመንግስታቱ ማህበር (League of Nations)፣ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እና የአፍሪካ ህብረት መስራች በመሆኗ እንዲሁም ጥቁር ህዝቦች ለነጻነታቸው ባደረጉት ትግል ከጎናቸው በመቆሟ በብዙ ወገኖች ዘንድ የነበራትን ዝናና ክብር በዓመታት በጦርነትና በረሃብ ስትሰቃይ የተረሳበት ወቅት ዛሬ የኋላ ታሪክ ነው::

ባለፉት አስራ ስምንት አመታት ኢህአዴግ ባደረገው ያላሰለሰ ጥረት ኢትዮጵያ ከራሷ አልፎ ለአፍሪካ ቀንድ ብሎም የመላው አፍሪካ ድምጽ እስከመሆን ደርሳለች:: መንግስት ከጎረቤቶቻችን ጋር ያለንን ችግሮች በሰከነ መልኩ በመፍታት ስኬታማ ተግባር አከናውኗል:: አለም አቀፉ ማህበረሰብ ከኢትዮ-ኤርትራ ጋር ያውን የድንበር ውዝግብ በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ ያቀረበውን የሰላም ሀሳብ እንዲደግፍ፣ በሶማሊያ ጉዳይም አዎንታዊ ሚና እንዲጫወት ተንቀሳቅሶ የተሳካ ዲፕሎማሲያዊ ድል ተቀዳጅቷል:: በአዲሱ የአፍሪካ የልማት አጋርነት (ኔፓድ) እንዲሁም ከአፍሪካ አንድነት ወደ አፍሪካ ህብረት በተደረገ ሽግግር ተሳታፊ ብቻ ሳይሆን ሀገራችን ንቁ ተዋናይ ናት:: ሀገራችን በዓለም አቀፍ መድረኮችም ከሰሀራ በታች ያሉ ሀገሮችን ለመደገፍ የቀድሞ የብሪታኒያ ጠ/ሚኒስትር ቶኒ ብሌዩር ከ6 ዓመት በፊት ባቋቋሙት የአፍሪካ ኮሚሽን ውስጥ የኢህአዴግ ሊቀመንበር የሆኑት ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ጉልህ ስፍራ ነበራቸው ብል ዕብለት ይሆንብኝ ይሆን? ከዚህም በኋላም በተለያዩ ሀገሮች በተካሄዱ የቡድን ስምንት እና ቡድን ሃያ ሀገሮች ስብሰባ ላይ ኢህአዴግ የሚመራው መንግስት የአፍሪካውያን ድምጽ ነበር:: ኮፐንሀገን ውስጥ በቅርቡ በተደረገው የአየር ለውጥ ስብሰባ ላይ ኢትዮጵያ አፍሪካን እንድትወክል መመረጧስ ምን ያሳየን ይሆን?

ኢትዮጵያ በአካባቢው ሀገሮች ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን በማድረግ ረገድ ጉልህ ሚና ያላት ሲሆን በአለም አቀፉ ማህበረሰብ የፀረ-ሽብር ዘመቻ ላይ ተደማጭ ናት:: በተጨማሪም ሀገሮች ሰላማቸው ደፍርሶ እንደሀገር የመቀጠል ሁኔታቸው አሳሳቢ ደረጃ ሲደርስ ኢትዮጵያ አይዟችሁ ባይናት:: አገራችን ባለፉት 50 ዓመታት በአለም ላይ

ለሰላም ማስከበር ወታደሮቻቸውን ከሚያሰማሩ 10 ሀገሮች ውስጥ አንደኛዋ ናት፡፡ ቀደም ሲል ሀገራችን ወደ ኮሪያ እና ኮንጎ በመዝመት ሃላፊነቷን መወጣቷ አይዘነጋም፡፡

ባለፉት ዓመታትም መንግስት ወደ ሩዋንዳና ቡሩንዲ ላይቤሪያ የመከላከያ ሰራዊታችንን በማሰማራት ሀገሮቹ ዳግም እንዲያንሰራሩ አፍሪካዊ ኃላፊነቱን ተወጥቷል፡፡ የሩዋንዳው ፕሬዚዳንት ፖል ካጋሜ በቅርቡ ለጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ኒሻን በሸለሙበት ወቅት እንደተናገሩት አገሪቱ አንድ ሚሊየን የሚሆኑ ዜጎቿን በጅምላ ጭፍጨፋ ስታጣ እምባቸውን ካበሱ ሀገሮች ኢትዮጵያ ቀዳሚ ነበረች፡፡ በሱዳን ዳርፉርም የፖሊስ ሃይል በማሰማራት ለሀገሪቱ ሰላም አስተዋጽኦ እያደረገ ይገኛል፡፡ እዚህ ላይ መጠቀስ ያለበት የቀድሞው የተ.መ.ድ ዋና ጸሀፊ ኮፊ አናን እንዳሉት የሰላም አስከባሪ ሃይል ፀጥታ ከማስከበር በዘለለ ለህብረተሰቡ ልማት በመሰማራት የተሸለ ሰላምና መረጋጋት የማስፈን ዕድል እንዳለው ያሳየው የመከላከያ ሰራዊታችን ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ገዢው ፓርቲ የሚመራው መንግስት በሰጥቶ መቀበል የሚደራደር ሲሆን በውስጥ ጉዳያችን አላስፈላጊወ ጫና የሚፈጥሩ ወገኖችን «በሊማሊሞ መሄድ ትችላላችሁ» የሚል መሆኑንም መዘንጋት አይገባም፡፡

## <u>ፅናት እና ዲሲፕሊን</u>

አንድ ፓርቲ መልካም ስትራቴጂና ፖሊሲ እንዲሁም ቅን አመለካከት ስላለው ብቻ በአንድ ሀገር ሰላምና ዲሞክራሲ እንዲሰፍን ልማት እንዲረጋገጥ አያስችሉትም፡፡ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ጥሩ ስትራቴጂና ፖሊሲ እንኳ አላቸው ቢባሉ ይህን የሚያስፈፅም የተደራጀ ኃይል የላቸውም፡፡ ብዙዎቹ ምርጫ መጣ ሲባሉ የሚሰባሰቡ በማግስቱ የሚበተኑ ናቸው፡፡ መሪና ተመሪው አይታወቅም፡፡ ለዓመታት ጠቅላላ ጉባኤም ሆነ የአመራር ምርጫ አካሂደው አያውቁም፡፡ ስም መጥራት ባያስፈልግም የእነዚህ ሙት ፓርቲ መሪዎች አንዴ ከተመረጡ በዚያው ይረሳሉ፡፡ ለመሆኑ እነሱ ጋር መተካካት የለም እንዴ? የፓርቲ ዲሲፕሊን የሚባል መሪውንም ተመሪውንም አያስጨንቀውም፡፡ ለእለት ፍጆታ እስኪረዳ ድረስ የተፈለገው ይወሰናል ይፈጸማል፡፡

በተቃራኒው ኢህአዴግ በፅናት፣ በኃላፊነት ስሜት እንዲሁም በዲሲፕሊን የሚንቀሳቀስ ፓርቲ ነው፡፡ በመሆኑ በቀጣዩ ምርጫ ለመመረጥ ያሚያስችሉት ከላይ የተጠቀሱት ጥንካሪዎቹ እንጂ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ድክመት ወይም ፋይዳ ቢስነት አይደለም፡፡ ኢህአዴግ የሚመረጠው የጠራ ተልዕኮ እና የሀገራችንን ልዕልና ማስከበር

የሚችል አቅም ያለው ድርጅት በመሆኑ ነው ። እኔ ኢህአዴግ ተወዳዳሪ ስለሌለው ያሳዝነኛል፤ ቢኖረውም ግን ያሸንፋል። የጠንካራና ሀላፊነት የሚሰማቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎችና መሪዎች መኖር በሀገሪቱ እየተካሄደ ያለውን የልማትና የዲሞክራሲ ስርዓት ይደግፉ ነበር። ሆኖም እኛም ኢህአዲግም ለዚህ አልታደልንም።